ክፍል2

# የአማራን ማንነት በአማራ ድርጅት

ከዚህ ከራሱ የአማራው መሰባሰቢያና መጠናከሪያ ድርጅት ውጭ የሚሞከሩ ሁኔታዎች እ/ሥከዛሬ የጠፋባቸውን፣ የተገደለባቸውን፣የተጋዘባቸውንና የተመታባቸውን መንገዶች መከተል ይሆናልና ጥንቃቄ ያሻል።

ይህንንም የአማራ አንድነት ሥብስብ ያላንዳች ማወላወል በማጠናከር፣በመርዳትና በመደገፍ ከጎኑ እንደምንቆም አልጠራጠርም ምክንያቱም ከሕዝቡ ጋር ካለው ትሥሥር አንፃር የሕዝቡም ትግል እንዲፋጠን፣ ሠቆቃውም እንዳይራዘምና የመኖር ዋሥትናውም እንዲረጋገጥለት ሥለሚጥር።
በውጭ ሀገራት የተፈጠሩ የአማራ ሥብስቦች በአንድነት መቆም አጠያያቂ አይደለም።ይህ ሲሆን ነው እርዳታችን ወይም ድጋፋችን አመርቂ የሚሆነው።

ዛሬ ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ቢኖር፣ኢትዮጵያ ውስጥ በኀበዝ አለቃም ሆነ በተለያዩ መንገዶች የአማራን ሕዝብ ትግል እያሥተባበራችሁና ለድል ለማብቃት አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ያደረሳችሁ ወገኖቻችን፣በአንድ መከራችሁ የአማራ ድርጅቶቻችሁን ወደ **አንድ ግዙፍ የአማራ አንድነት ድርጅት** አምጥታችሁ በመግለጫም ይሁን በሌላ መንገድ ዓለም እንዲያውቀው ብታደርጉ ይመረጣል።

ይህንን ለማድረግ ጊዜ የሚያሥፈልገው ከመሰላችሁ ተቀራርባችሁ እንደምትሰሩ የሚያመላክት ወይም የሚያበሥር ጊዜያዊ የሆነ **"የአማራ ድርጅቶች ህብረት እ/ሥከውህደት"** የሚል በአስቸኳይ መፍጠርና በመግለጫ ለሕዝብ ማሳወቅ ለነገ የሚባል አይደለም።
ይህንን ሥታደርጉ ነው አማራው ትልቅ አይበገሬ ኃይል ሆኖ የሚገኘው፣የአማራው ጠላቶችም አፍራሽ ተልዕኮ የሚገታው ።

ይህን በአፋጣኝ ሳታደርጉ ከዘገያችሁ "ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል" እንደሚባለው፣እ/ሥከዛሬ አማራነትን ለማጥፋት ሲታገሉን የነበሩት አፍራሽ ኃይሎች "ባለቤት የሌለው ቤት" ሥለሚመስላቸው የአማራውን ትግል ለመጥለፍ ከመሯሯጥ አይቦዝኑም ። አማራው! ይህንን አሸንፎ መውጣት ከተሳነው መጥፊያው እንደሚሆን መዘንጋት የለበትም።

አማራው በአማራነት ብቻ እራሱን እያጎለበተ በሄደ ቁጥር፣ዘረኞቹን የትግሬ ወራሪዎች ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥልጣን አሽቀንጥሮ መጣልና ጠራርጎ ማባረር እንደሚችል በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የሰቆቃውንም ጊዜ ያሣጥራል።

የኦሮሞ ድርጅቶች ለኦሮሞ መቆማቸውን ግልፅ አድርገው ሥለሚታገሉ፣ ለንግግርም ሆነ ለቃለመጠይቅ የሚጋብዟቸው ቡድኖች እንኳን ልምምጥንና አክብሮትን ባዘለ መልኩ ሲያስተናግዷቸው ተመልክተናል።

ኢትዮጵያ ውሥጥ የአማራም ድርጅት ለአማራ መቆሙን ግልፅ አድርጎና ጠንክሮ ከወጣ ከግራም ከቀኝም አክብሮት ይመጣል። ይህ ሲሆን ነው ቡድኖቹ የኦሮሞን ትግል ለመቦርቦርና ጣልቃ ለመግባት እንዳልደፈሩት ሁሉ የአማራውንም ትግል የማይደፍሩት። ለዚህ ተግባራዊነት ጠንክረን እንሥራ።

የአማራው ወጣት ትግሉን እያካሄደ "የኦሮሞ ደም የኔ ደም ነው"ሲል፣የኦሮሞው ወጣትም "የአማራው ደም የኔ ደም ነው" ሲል ተደምጧል።እንዲህ ዓይነት መልዕክት ከሁለቱም ጎራ የተሰማው የጉዳዩ ባለቤቶች የአማራና የኦሮሞ ወጣቶች በመሆናቸው ነው።እንዲህ ዓይነት መልዕክት ለአያሌ ዓመታት ተሞክሮም አያውቅም።

ለዚህ ሁሉ ምክንያቱ በ70ዎቹና በ80ዎቹ ካለፍነው ውሥጥ የመለያየት አባዜ የተጠናዎተን በመኖራችን ነው።
ምናልባት ይህ አገር ያፈረሰና ሕዝብን ከሕዝብ የለያየ ቡድን፣
(1ኛ)ጣልቃ እየገባ ትግሉን ካልበጠበጠውና ካልበከለው፣
(2ኛ)በወጣቱም ዘንድ ተቀባይነት ካጣ
(3ኛ)በዕውነት እነኚህ ወጣቶች ይበልጥ ከተቀራረቡና አብረው ከታገሉ አገርም አገር፣ሕዝብም ሕዝብ የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ይሆናል የሚል ተሰፋ መሰነቅ የግድ ነው።አንድነቱን የማምጣቱም ተሥፋ ይኖራል።

ይህ ተግባራዊ እንዲሆን ከአንጋፋዎቹ ማለትም ከቆየነው የሚጠበቀው እንደ እሥከዛሬው "እንምራህ" ሳይሆን፣ ትግሉን ያቀጣጠለው ወጣት የትግል ባለቤትነቱን ሥለያዘ፣ትግሉን እየመራ ግብ እንዲያደርሰው ከጎኑ በመቆም ማበረታታትና አሥፈላጊውን ምክርና ዕርዳታ ማቅረብ ነው።አንጋፋው ቡድን የወጣቱን ትግል ነጥቆና ቀልብሶ ከወያኔ ጋር ሥልጣን እይዛለሁ ካለ ጉድ ይፈላበታልና ያስብበት።

<u>የኢትዮጵያ አንድነት</u>

ዕውነት መራራ ሥለሆነች ሀቁ እንደሚያመን ብረዳም "መነሻውን ያላወቀ መድረሻውንም እንደማያውቅ" መጠቆም የግድ ነው።ሥለሆነም አልሰማንም ብለን ጆሯችንን ካልደፈን፣አላየንም ብለን ዓይናችንን ካልጨፈን፣ዕውነትን በውሸት፣ሀቅን በክህደት ካልተካን በሥተቀር፣የኢትዮጵያ አንድነት የተናደው ወያኔ ገብቶ የሽግግር መንግሥት ተብየውን ካቋቋመበት ከ1983ዓ.ም.ጀምሮ ነው።

የኢትዮጵያ አንድነት ብሎ ለመጥራት የሚያሥደፍረው አማራው፣ኦሮሞው፣ጋምቤላው፣አፋሩ፣ጉራጌው፣ከምባታው፣ ሀዲያው ወዘተ በአንድነት ጎራ ቢቆሙ ነበር።

ይህ በ1983ዓም ከአማራው በሥተቀር ሁሉም ጎሳዎች በየጎሳቸው ሲቆሙ አከትሟል።ወያኔ አማራን የማጥፋት፣አገር የማፍረስና ሠርቆ የመውሰድ የቤት ሥራውን በ25ዓመታት ሲያገባድድ፣አማራው ብቻውን ከተወሰኑ የየጎሳዎቹ ሰዎች ጋር በሰላማዊ መንገድ የኢትዮጵያ አንድነት እያለ መቀጠሉ በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ ነው።

ለማንኛውም ከፊሎቹ ወገኖች ተጨባጩን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማሥገባት ጥረት የሚያደርጉት፣ የተናደው የኢትዮጵያ አንድነት ከጊዜና ከሁኔታ ጋር እንደገና ሊመጣ ይችል ይሆናል በሚል ተሰፋ ነው።

ይህን አሥተሳሰብ የሚያራምዱ ቡድኖች በሌሎች ጎሳዎች ብቻ ሳይሆን፣በአማራው ላይም የሚደረገውን የዘር ማጥፋት ዘመቻ የሚያወግዙና አማራው ለመብቱ መቆም እንዳለበት የሚቀበሉ ሲሆኑ፣ አማራውም በሚያካሄደው ትግል ላይ ተፅዕኖ ሥለማያደርጉበት በአክብሮት ይመለከታቸዋል።

ከፊሎቹ ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ በጎሳ ተከፋፍሎ ምሥቅልቅል ሁኔታ ተፈጥሮ እያንዳንዱ ጎሳ የየግሉን ክልልና ባንዲራ ተብዬውን ታቅፎ የሙጥኝ ባለበት ወቅት፣ከአፍ ያለፈ አንድነት እንደሌለ ተጨባጩ ሁኔታ ቁልጭ አድርጎ ቢያሳያቸውምና ቢገነዘቡም፣ቀፎውን የቀረ የአንድነት ዋሻ ውስጥ ገብተው፣ በኢትዮጵያ አንድነት ሥም ሽምጥ ሲጋልቡ ይሥተዋላሉ።

እነኚህ ከአማራ አብራክ የተፈጠሩ ቡድኖች፣ከአማራው ውጭ ያሉ ጎሳዎችን እያቀማጠሉ፣ አማራውን ለገንዘብ ምንጭነት፣ለአጃቢነትና ለሥልጣን መቆናጠጫነት ሥለሚፈልጉት፣አማራው ለአማራነት ማንነቱ እንዳይታገል የተለያዩ አሻጥሮችና ተንኮሎች እየሸረቡ ፣ 25ዓመት የተጠቃበትን መንገድ ተከትሎ እንዲያልቅ እየታገሉት ይገኛሉ።

በንቃተ ህሊና ጉድለት ምክንያት ትናንት መዐሕድን አሥበልተናል፣ዛሬ ደግሞ አማራው በአማራነት እንዳይሰባሰብ፣ እንደከዚህ ቀደሙ በረቀቀ መንገድ በአንድነት ሥም እየማሉ፣ "አማራ አትበሉ፣የኢትዮጵያ አንድነት በሉ" እያሉ 25ዓመታት የጠላት መሳሪያ በመሆን አማራውን ሲጠቀሙበትና ሲያስጠቁት የኖሩ ቡድኖች፣ዛሬም አልተኙም።

ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አማራውን ትጥቅ ለማሥፈታት እንደትናንቱ ከፊት ከፊቱ ቀደም ቀደም እያሉ አሁን የተቀጣጠለውን የአማራ የማንነት ጥያቄ ለመጥለፍና ለመቀልበስ ብሎም በቁጥጥራቸው ሥር ለማድረግ የተቻላቸውን ያህል እየጣሩ ይገኛሉ። እነኚህ ኃይሎች!ወጣቱ ለማንነቱ ሲዋደቅ፣ለጠላት ዱላ ያቀብላሉ።

እነኚህን በከፊልም ቢሆን፣ለአማራው ዘር መጥፋት ከተጠያቂነት የማያመልጡ ትውልደ አማራ ቡድኖች፣ዛሬ በዱር በገደል እንዲሁም በየእሥር ቤቱ ፍዳውን የሚያየው አማራ ጊዜ መሥተዋት ነውና፣ ጊዜና ሁኔታው ሲመቻች ከተጠያቂነት አያመልጡም።

አማራነት በመወለድ ብቻ ሳይሆን ለአማራው ከገንዘብ ጀምሮ እሥከህይወት መሥዋዕትነት ለመክፈል በቁርጠኝነት መቆምንና መሥራትን ይጠይቃል።

**ወጣቱ ለማንነቱ ሲዋደቅ፣እየረዳነው ነው ወይስ ለጠላት ዱላ እያቀበልን?**

በአፄ ኃይለሥላሴም ሆነ በደርግ ጊዜያት በ70ዎቹና በ80ዎቹ፣ በነበሩት ትግሎች ብዙሀኑ በቅንነት ጥሩ ነገር ለማምጣት ጥሯል።ነገር ግን ሁላችንም ማለት ይቻላል ብዙ ሙከራዎች ብናደርግም ፈተናውን ያላለፍንና የወደቅን ሥለሆነ ቆም ብለን ራሳችንን እንድንመርምር እጋብዛለሁ።

ዛሬ መሥዋ ዕትነት እየከፈለ የሚታገለው የአማራ፣የኦሮሞ ወዘተ ወጣት! ከወያኔም በፊት ሆነ በወያኔም ዘመን የጥፋት ድርሻ ያለውን ፣እንዲሁም ለዳግመኛ ጥፋት በቪዥን ኢትዮጵያ"ኢትዮጵያዊነት የለም" የሚለውን የ70ዎቹና የ80ዎቹ ትውልድ እንዲመራው አይፈልግም። ወጣቱ ምሩን፣ወክሉን ሳይል፣ እንመራሀለን፣እንወክልሀለን ባንለው ይመረጣል።

አሁን የሚካሄደውን ትግል እንምራ ካልን እንደገና ውድቀት ሥለሚሆን፣የሚመረጠው ጣልቃ ሳንገባበት አሁን ወጣቱ የሚያደርገውን እየተከተልን፣ ወጣቱ "ምክር ለጋሽ እፈልጋለሁ" ካለ ምክር መሥጠት፣መሥሎ የሚታየንን ሀሳብ መሠንዘር፣ለትግላችን ይጠቅማል የሚሉትን ይቀበሉታል፣ካልጠቀማቸው አይቀበሉትም።

ሥለዚህ ወጣቱ ለማንነቱ ሲዋደቅ፣ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እንርዳው ፣ከጎኑም መቆማችንን በተግባር እናሳይ።

**<u>ትልቅ መልዕክት፣ ወገናችንን ለመታደግ ኢትዮጵያም ሆነ ውጭ አገር በአማራ ድርጅት ለተቋቋማችሁ ወገኖች!!!</u>**

ለአንድ ዓላማ በቆማችሁት ድርጅቶች መካከል፣ የድርጅት ፍቅር አይሎ "እኛ አይደለንም፣እነሱ ናቸው" ወዘተ የመባባል የእርስ በእርስ መጓሸምና የመጠፋፋት አሉባልታ፣በ70ዎቹና በ80ዎቹ እንደሆነው እንዳይመጣና የወገናችንን ትግል እንዳናስበላው መጠንቀቅ ያሻል።

ይህንን ማድረግ ከተሳናችሁ ዛሬ የሚደግፋችሁም ሕዝብ ድጋፉን ያነሳል።ድርጅቶቹም ያለጥርጥር ከጊዜ ጋር ወዳቂዎች ይሆናሉ።

ይህ ደግሞ በኢሕአፓና በመኢሶን ቀጥሎም በቅንጅት ታይቷል።በዚህ መካከል የሚጎዳው በወያኔ ጦር የታወጀበት ወገናችን እንደሆነ መገንዘብ ያሥፈልጋል።

"ከኋላ ወዬው ጠንቀቅ ብለህ ቆዬው" እንደሚባለው፣ይህ ከሁሉም በላይ ቀዳሚውንና ወሳኙን ቦታ ሥለሚይዝ እንደቀላል ነገር አንብቦ የሚታለፍ ሳይሆን ለዚህ ቁምነገር ትልቅ ቦታ ሠጥታችሁ በተግባር እንድትተረጉሙት አደራችን የጠበቀ ነው።

ይቀጥላል